# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፦ ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## <u>ዜና ዘገባ</u>

**ሐምሌ 24 ቀን 2002**

**መለስ የአፍሪካ መሪዎች ለቻይና እንዲያጎበድዱ አጥብቆ እየሰራ ነው ተባለ፤**

**ለዘመናት ተከብሮ የኖረው የአራት ኪሎ ቤተ መንግስት ደኖች ተጨፈጨፉ፤**

**የወያኔ ቡድን ከኦጋዴን ነፃ አውጭ ግምባር ጋር የሰላም ስምምነት ተፈራረምኩ ይላል ሁኔታው ግን ተባብሰዋል**

ከበረሀ ጀምሮ የገዛ ጓደኞቹን ተራ በተራ እየፈነገለ እዚህ የደረስው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ እንደለመደው ዛሬም የአፍሪካ መሪዎችን እርስ በርስ እያናከሰ የራሱን ዝና በማግሰበስ ላይ መሠንበቱ ታውቋል::

በኡጋንዳ ዋና ከተማ ካምፓላ የመሪዎች ስብሰባ ከሐምሌ 18 ቀን እስከ ማክሰኞ ሐምሌ 20 ቀን 2002ዓ.ም. ድረስ የተደረገ ሲሆን በዛ ስብሰባ ላይ ዋነኛ አጀንዳ ተብሎ ሲጠበቅ የነበረው ተትቶ ሌላ አጀንዳ ላይ ሲነታረኩ መሰንበታቸው ታውቆዋል::

ከኡጋንዳው መሪ ዮዌሪ ሙሴቬኒ ጀምሮ እስከ ወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ድረስ ህዝቦቻቸውን ለርሀብ እና ለእርዛት ዳርገው የራሳቸውን ስልጣን ለማራዘም ብሎም ዝናቸውን የሚያስጠብቁትን መላ ሲወያዩ ከመሰንበታቸውም በተጨማሪ አንዱ አንዱን እያሞካሸ እርስ በእርስ ሲሸዋወዱ መሰንበታቸው ታውቋል::

መለስ ዜናዊ አምና የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ ላይ የአፍሪካን ተላላኪነት ተሰጥቶት የነበረ ሲሆን ዘንድሮ ይህንኑ ቦታ ይለቃል ተብሎ የተጠበቀ ቢሆንም አስቀድመው ለሆዳቸው ያደሩ መሪዎችን በገንዘብና በጥቅማጥቅም በማሰሩ ያለ አንዳች ግርግር መልሶ ቦታ ለመያዝ ችሏል፡፡

በሀገርና ህዝብ ላይ ግፍና በደል እየሰራ የሚገኘውን አምባገነኑን መለስ ጥቂት የአፍሪካ መሪ-ዎች ድጋፍ ቢሠጡትም ቁጥሮቻቸው ቀላል ያልሆኑት ተቃውሞም ሆነ ድጋፍ ሳይሰጡ በድምፀ ተአቅቦ መውጣታቸውን የጠቆመው የደረሰን ዘገባ በተለይም እስልምና ተከታይ የአፍሪካ መሪዎች መለስ በሱማሊያ ላ በሚፈፅው ድርጊት የተነሳ ከፍተኛ ጥላቻ እያሳዩ እንደነበርም የደረሰን ዘገባ አጋልጧል፡፡

ከቻይና ጋር እፍ ንፍስ ያለ ፍቅር ላይ የወደቀው መለስ ዜናዊ የአፍሪካ ሀገራት መሪዎችን እንደራሱ የጠበቀ ግንኙነት እንዲፈጥሩ ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ ላይ መሆኑን የጠቆመው ዘገባ በተለይ ማዕድን አውጪ የአፍሪካ ሀገራት ከቻይና ጋር ጥብቅ ትስስር እንዲኖራቸው ለማድረግ አጥብቆ እየሰራ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡

ለቻይና ያጎበደደው መለስ ዜናዊ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡትን ቻይናዊያን እየተለማመጠ ዓለም አቀፍ ህግን በጣስ መልክና የሀገርን ጥቅም በሚጎዳ ሁኔታ ያለ አንዳች ግብር በሀገሪቱ እንዳሻቸው እንዲፈነጩ ከማድረጉም በተጨማሪ ዛሬ ከከፍተኛ ባለሀብት ጀምሮ እስከ የቀን ስርቶ አደር የሆኑ ቻይናውያን ድረስ እየተሰገሰጉ የዜጎችን ስርቶ የመኖር ህልውና እየተጋፉ ይገኛሉ፡፡

ይህ አልበቃ ብሎት የአውሮፓ ሀገራትንም በሙሉ ከቻይና ስር ለማንበርከክ ሌት ተቀን ከመሮጡም በላይ የምዕራብ ሀገር ደጋፊ ናቸው የተባሉ የአፍሪካ ሀገራት መሪዎችን ሀሳብ እያስለወጠ መክረሙንም ለዲፕሎማቲክ ቅርበት ያላቸው ወገኖች እየገለፁ ነው፡፡

ነጭ ሲሉት ጥቁር ......ሰማይ ሲሉት ምድር .....የሚገኘውና እንደ እስስት ባህሪውን እየቀየረ ያለው ይኽ አረመኔው ግለሰብ ዛሬ ዜጎች በስራ እጦት የእለት ጉርስ ለማግኘት በተቸገሩበት በዚህ ወቅት በውምብድና አስራቸው የነበሩት ዜጎቿን እየፈታች ለቀን ስራ ሳይቀር ወደ ኢትዮጵያ እየሰገሰገች መገኘቱዋም የነመለስ ዜናዊ መሰሪ ስራ መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

ከስፍራው ሾልኮ የደረሰን ጥብቅ ሚስጥር እንዳመለከተው ከሆነ እስከ ዛሬ ነጋዴዎች ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡት ዕቃች የተለያየ ሀገር ስሪት የነበረ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ከቻይና ስሪት በስተቀር ከሌላ እንዳያስገቡ የተከለከለ መሆኑን ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀው ምናልባት የሌላ ሀገር በተለይ የምዕራብ ሀገራት ስሪት የሆነ እቃ ቢመጣ ጉምሩክ ታሽጎበት እንዲቀር አልያም የቀረጥ ክፍያው እጅግ ከባድ እንዲሆን መደረጉንም ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በዚህም ምክንያት ከግለሰብ እስከ መንግስታዊ ተቋም ድረስ በተሰጠው ጥብቅ ምስጢራዊ ትዕዛዝ መሰረት የቻይና ስሪት የሆኑ እቃች ለመግዛት እንደተገደዱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በቅርቡም ለመላው ሀገሪቱ የሚሆን የመብራት ሀይል መቆጣጠሪያ ጋኖች በውድ ዋጋ ከቻይና ተገዝተው ስራ ላይ የዋሉ ቢሆንም እዚህ ግባ የማይባል አገልግሎት ሳይሰጡ እየተበላሹ የመብራት ስርጭቱ ተቋርጦ ዜጎች በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ለመኖር ተገደዋል::

ገበሬውን በነፃ ያለአንዳች ክፍያ እያፈናቀሉ ኢንቨስተር ነን እያሉ ለሚመጡ ቻይናውያኖች መሬት በነፃ እያደሉ መሆኑን የተገነዘቡ ምሁራኖች በዜጎች ላይ እየተፈፀመ ያለውን ሰብዓዊ መብት ጥፋት ብቻ ሳይሆን የመኖርና ያለመኖር ህልውና የሚፈታተን እርምጃ ነው በማለት እያወገዙ ይገኛሉ::

ከአፍሪካ ይልቅ ቻይና የበለጠችበት መለስ ዜናዊ ሰሞኑንም የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝዳንት ታቦ ኢምቤኪ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የክብር ዶክትሬት ተሸላሚ አድርጎ የሸለማቸው ቢሆንም በዕለቱ በቤተ መንግስት ውስጥ ተቀምጦ ከቻይና ባለሀብት ነን ከሚባሉ ሰዎች ጋር አብሮ የዋለ መሆኑንና በበዓሉ ላይ ሳይገኝ እንደቀረ ለማወቅ ተችሎዋል::

በአንድ ወቅት በአፍሪካ ምርጥ እና ስመ ገና ከሆኑት መሪዎች ግንባር ቀደም እና ለአፍሪካውያኖች አለኝታ ናቸው ተብለው ሲወደሱ የነበሩት ታቦ ኢምቤኪ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለተበረከተላቸው የክብር ዶክትሬት ሽልማት ላይ አለመገኘቱ የጥቁር ህዝቦችን መናቁን በግልጽ ያሳየ የቻይናዎች አጎብዳጅ መሆኑን ያረጋገጠ ነው ሲሉ ብዙ ምሁራኖች እየተቹት ይገኘኛሉ::

ለዘመናት ተከብሮ የኖረውንና የቤተ መንግስት ውበት የነበረው እድመሜ ጠገብ ዛፎች ተጨፍጭፈው እንዲወድሙ መደረጉን በአይን ለማረጋገጥ ተቻለ::

ከአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት ጀምሮ ከ100 ዓመታት በላይ ሲወርድ እና ሲወራረድ የመጣው ይሄው የዛፍ ደን በአግባቡ እንክብካቤና ጥበቃ ሲደረግለት የቆየ ቢሆንም ሰሞኑን በሚያሳዝን ሁኔታ ያለ አንዳች ምትክ ተጨፍጭፈው እንዲጣሉ መደረጉን ታወቀ::

ምንም ዓይነት መተኪያ ሳይደረግለት በአራት ኪሎ ቤተ መንግስት ግቢ ውስጥ እና ከአጥር ውጭ የነበሩት ደኖች ለቤተ መንግስቱ ውበት ከመሆናቸውም በተጨማሪ በአካባቢው ንፁህ አየር እንዲኖር ትልቅ አስተዋፅኦ ሲያበረክቱ የኖሩ ቢሆንም ሰሞኑን የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ሙሉ ለሙሉ ከጥቅም ውጭ እንዲሆኑ መደረጉን እና የቤተ መንግስቱ ታሪካዊ ቅርስነት ጨርሶ እንዲጠፋ ማድረጉ ታውቆዋል::

ጥፋትን እንጂ ልማትን ከቶ የማያውቁት ከቶ የማያውቁት እነ ወዲ ዜናዊ ለዘመናት ተከብሮ የኖረውን አስጠብቆ እና ታሪካዊ ቅርስነቱን መጠበቅ ሲገባቸው በማን አለብኝነት አንድም ምትክ ዛፍ ሳይተክሉ መጨፍጨፋቸው እጅግ የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን የሚያበሳጭ መሆኑን የገለፁት በቤተ መንግስቱ ዙሪያ ለብዙ ዓመታት ነዋሪ የሆኑ የአካባቢው ህብረተሰብ ያንን የመሰለ ውብ ግቢ ቅርስነቱ እንዲጠፋና ብሎም እንዲበላሽ ሆን ብለው የሰሩት ሸፍጥ ነው በማለት በቁጭት ሲናገሩ ተደምጠዋል::ከቅርብ ግዜ ወዲህ እርስ በርስ መተማመን ያጡት እና አንደኛው አንዱ ጥላ ሆነው እየተከታተሉት የወያኔ ባለስልጣናት ፍርሀት ውስጣቸው በመንገሱ በተለይ መለስ ዜናዊ ከፍተኛ ፍርሀት ውስጥ በመውደቁ ዙሪያውን 16 ዘመናዊ የጥበቃ ማማዎች በከፍተኛ ወጪ ከማሰራቱም በተጨማሪ በ3 ዙር ጥበቃ እየተጠበቀ መሆኑን የጠቆሙት ውስጥ አዋቂ ምንጮች በግቢ ዙሪያ

የሚደረገውን እንቅስቃሴ በካሜራ ለመቅረጽ እንዲያመቸው ሙሉ ለሙሉ ዛፎቹ እንዲጨፈጨፉ መደረጉን ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በመላው ዓለም ላይ የደን ሀብቶች እየተመናመኑ በመምጣታቸው ዓለም አቀፍ ደረጃ የአየር ንብረት መዛባት በተከሰተበት እና ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት የዛፍ ተከላ ዘመቻ በሚደረግበት በአሁኑ ሰዓት ለዘመናት ተከብሮ የኖረውን የቤተ መንግስት ባህር ዛገፍ፤ሾላ፤ዝግባ፤ወይራ፤ዋርካ፤እና መሰል ዛፎች እንዲጨፈጨፉ መደረጋቸው የሚያሳዝን እና የሚያስቆጭ ነው ሲሉም የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በቁጭት ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

የወያኔ ቡድን ከኦጋዴን ነፃ አውጭ ግንባር ጋር የሰላምና የእርቅ ስምምነት ሐምሌ 22 ቀን 2001 ዓ.ም በግዮን ሆተል ሳባ አዳራህ መፈራረሙን ቢገለጽም በስፍራው ያለው ችግር ተባብሶ መቀጠሉን ከጅጅጋ የደረሰን ዘገባ ገልጧል፡፡

የወያኔ ቡድን ባለስልጣን የሆነው እና በኮታ ስልጣን የተሰጠው የፌዴራል ጉዳዮቸ ሚኒስትር ዶ/ር ሽፈራው ተክለ ማርያም የተባለው ሲሆን ከነፃ አውጭው ተብሎ ደግሞ አቶ ኢብራሂም መሀመድ ሁሴን ነው ተብሏል፡፡ ኦብነግ በተለያዩ ምክንያቶች ያባረረው እንደሆነ የተነገረለት ይህ ግለሰብ በክልሉ ሲከሄዱ በነበሩ ግጭቶች የሰብአዊ ጉዳቶቸ እጅግ የከፉ እንደነበሩ ዘርዝሮ ድርጅቱ ከወያኔ ጋር በተደጋጋሚ ድርድር ማድረጉንና ሆኖም ፍሬ ሳያገኙበት መቆየቱን ገልጧል፡፡ ድርጅቱ ሰላም የእድገት ቁልፍ መሆኑን መገንዘቡን የጠቆመው አቶ ኢብራሂም ሁለቱም ወገኖች በጉልበትና በጦርነት የሚፈታ ችግር አለመኖሩን ተገንዝበው በሰላማዊ ድርድር በቅንነት መነሳታቸውን አሳውቀዋል፡፡ በአፍሪና በአውሮፓ የታዩት ሁኔታዎች ይህ ጅምር የሚጠናከሩ ናቸው የሚለው አቶ ኢብራሂም ለሶስት ወር የተደረገው የተኩስ ማቆም ስምምነት የክልሉን ሕዝብ አገኝቶ ለማነጋገርና የሰላም ስምምነቱን ጠቀሜታ ለማሳወቅ እንዳገለገላቸው ቢናገሩም በዚህ ሳምንተ በተለይ ስምምነቱ በግዮን ሆተል ተፈራረሙ በተባለበት ዕለት በኦጋዴን የተለያዩ ክፍሎች ግጭት መቀስቀሱን የደረሰን ዘገባ አጋልጧል፡፡ በስምምነቱ ብዙ ጥቅመ አግኝተናል እያለ የሚለፍፈው ይሔው ኢብራሂም የተባለው ግለሰብ ለወያኔ ያደሩትን ብቻ በመሰብሰብ ያደረገው ስምምነት ከልሆነ በስተቀር አንዳች ም ውጤት ያልታየበት መሆኑም ታውቋል፡፡ በክልሉ በተከሰተ አዲሰ ውጥረትም ምንያት የወያኔ ቡድን ግዙፍ ጦር ወደ ዚያው የላከ መሆኑንነም ከአይን እማኞች ገለፃ ለመረዳት ተችሏል፡፡